# ልጅዎን በትምህርት ቤት ውስጥ ለማገዝ ማወቅ ያለብዎት ነገሮች

## ለወላጆች፣ ለአሳዳጊዎችና ለተንከባካቢዎች መምሪያ



በመኖሪያ ቤት መጥፋት ምክንያት ቤተሰብዎ በጊዜያዊ ወይም በቂ ያልሆነ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ከሆነ፣ ልጅዎ ለተወሰኑ የትምህርት መብቶች እና አገልግሎቶች ብቁ ሊሆን ይችላል።

# የማኪኒ-ቬንቶ አገልግሎቶች ለማግኘት መስፈርቶች

ቤተሰብዎ በሚከተሉት የሚኖር ከሆነ፡-

- በመጠለያ ውስጥ፤
- አማራጭ በቂ መጠለያ ባለመኖሩ በሞቴል ወይም በካምፕ ውስጥ፤
- በመኪና፣ በመናፈሻ፣ የተተወ ህንፃ ወይም አውቶቡስ ወይም ባቡር ጣቢያ ውስጥ፤
- በመኖሪያ ቤት መጥፋት ወይም በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ከሌሎች ሰዎች ጋር በደባልነት፤

ልጅዎ የማኪኒ-ቬንቶ ሥርዓት ተብሎ በሚጠራው የፌዴራል ሕግ መሰረት እገዛ ሊደረግለት ይችላል።

# የማኪኒ-ቬንቶ መብቶች እና ድጋፎች

የእርስዎ የማኪኒ-ቬንቶ ብቁ የሆኑ ልጆችዎ የሚከተሉትን መብት አላቸው

- ነፃ፣ ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት ማግኘት።
- ምንም እንኳን በመደበኛነት ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ ሰነዶች ባይኖሩም ወዲያውኑ በትምህርት ቤቱ መመዝገብ።
- ትምህርት ቤቱ አስፈላጊ ሰነዶችን እየሰበሰበ ሳለ በትምህርት ቤቱ መመዝገብ እና ትምህርቶችን መከታተል።



- በአካባቢው ትምህርት ቤት መመዝገብ፤ ወይም ምርጫዎ ያ ከሆነ፣ በመጀመሪያ ትምህርት ቤቱ (በቋሚነት በቤት ሲቆዩ የተከታተሉበት ትምህርት ቤት ወይም በመጨረሻ የተመዘገቡበት ትምህርት ቤት) መከታተላቸውን መቀጠል።

  **የትምህርት ድስትሪክቱ የመረጡት ትምህርት ቤት የልጅዎ ምርጥ ምርጫ አይደለም ብሎ ካመነ፣ ድስትሪክቱ ስለ አቋሙ የጽሁፍ ማብራሪያ ሊሰጥዎ እና በውሳኔው ይግባኝ የማለት መብትዎን ማሳወቅ አለበት።*

- ይህንን ከጠየቁ፣ ወደ መጀመሪያ እና ከመጀመሪያ ትምህርት ቤቱ መጓጓዣ መቀበል።
- በልጆቻችሁ ፍላጎት መሰረት ለሌሎች ተማሪዎች ከሚሰጡት ጋር የሚወዳደር የትምህርት አገልግሎቶችን መቀበል።

# በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

## እኔ ስዘዋወር፣ ልጄን በተመሳሳይ ትምህርት ቤት ማቆየት አለብኝ ወይስ ልጄን ወደ አካባቢው ትምህርት ቤት ማስተላለፍ አለብኝ?

ከአንድ ትምህርት ቤት ወደሌላው መዘዋወር ልጆችን የሚረብሽ ሁኔታ ሊሆን ይችላል። የሚያውቋቸውን ጓደኞቻቸውንና መምህሮቻቸውን መተውና አዳዲስ ጓደኞች፣ አዳዲስ አስተማሪዎችንና አዲስ ክፍል መልመድ ይኖርባቸዋል። በዚህ ምክንያት ወደሌላ ቦታ ቢዛወሩ እንኳ ብዙውን ጊዜ ልጅዎ እዛው ትምህርት ቤቱ/ቷ (ትምህርት የጀመረበት) ቢቆይ ለልጁ ጥሩ ይሆናል።

ቦታ በሚቀይሩ ጊዜ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማሰብ ልጅዎ የድሮ ትምህርት ቤቱ መቀጠል አለበት ወይስ አካባቢዎ ወዳለው አዲስ ትምህርት ቤት መዛወር አለበት ለሚለው ሀሳብዎ ውሳኔ እንዲሰጡ ይረዳዎታል።



- ልጅዎ እድሜው ስንት ነው?
- አሁን ያለህበት የመኖሪያ ሁኔታ ምን ያህል ቋሚ ነው? ወደ መጀመሪያ ትምህርት ቤቱ ተመልሰው ለመዘዋወር አቅደዋል ወይንስ አሁን ካሉበት የመኖሪያ ቦታ አጠገብ የሚቆዩ ይመስልዎታል?
- ልጅዎ ከመጀመሪያ ትምህርት ቤቱ/ቷ ጋር የተያያዘ/ች ነው/ች? ከመጀመሪያ ትምህርት ቤቱ ጋር በጣም እንደተገናኘ የሚሰማው እና/ወይም ሊመረቅ ያለ ትልቅ ልጅ፣ ትምህርት ቤቶችን መለወጥ የበለጠ አስቸጋሪ ጊዜ ሊገጥመው ይችላል።
- መዘዋወር ስላለብዎት ልጅዎ ምን ያህል ይጨነቃል? ትምህርት ቤቶችን መለወጥ በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል?
- ትምህርት ቤቶችን መቀየር ልጅዎ ከትምህርት ቤት ወደ ኋላ እንዲቀር እና መጥፎ ውጤት እንዲያመጣ ያደርገዋል?
- ለምሳሌ በሴሚስተር ወይም በትምህርት አመት መጨረሻ፣ ከፈተና በኋላ፣ ወይም ለልጅዎ አስፈላጊ የሆነ ዝግጅት ካለቀ በኋላ፣ ይህ ለልጅዎ ትምህርት ቤቶችን ለመለወጥ ጥሩ የአመቱ ጊዜ ነውን?
- ልጅዎ ወደ መጀመሪያ ትምህርት ቤቱ በመመላለስ ምን ያህል ጊዜ ማሳለፍ አለበት? ረጅም ጉዞ በልጅዎ የትምህርት ቤት ስራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል።
- ልጅዎ በየትኛው ትምህርት ቤት መከታተል እንዳለበት በሚመርጡበት ጊዜ ሊያስቡባቸው የሚገቡ የደህንነት ጉዳዮች አሉ?

## እኔና ትምህርት ቤቱ ልጄ የት ትምህርት ቤት መሄድ እንዳለበት ካልተስማማን?

እርስዎና ትምህርት ቤቱ ካልተስማማችሁ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር እርስዎ እንደፈለጉት ሳይሆን ልጅዎ ሌላ ትምህርት ቤት እንዲገባ ለምን እንደወሰነ የሚያብራራ ሀሳብ በጽሑፍ ሊሰጥዎ ይገባል። አስተዳደሩ ይህንን ሀሳብ በመቃወም እንዴት ሀሳብዎን ሊያቀርቡ እንደሚችሉም በጽሑፍ ሊገልጽልዎ ይገባል። ቅራኔው መፍትሔ እስኪያገኝ ድረስ ለልጅዎ ጥሩ ነው ብለው ባሰቡት ትምህርት ቤት ልጅዎ መማር እና በትምህርት ቤቱ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ ይችላል።

## የልጄን ትምህርት ለመርዳት ማንን ማነጋገር እችላለሁ?

- እያንዳንዱ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት **የአካባቢው መጠለያ የሌላቸው የትምህርት ተጠሪ** አለው። ይህ ግለሰብ የትኛው ትምህርት ቤት ለልጅዎ የተሻለ እንደሚሆን እንዲወስኑ እና ከትምህርት ቤቱ ጋር እንዲነጋገሩ ይረዳዎታል። የአካባቢ ተጠሪ የትምህርት ቁሳቁሶችን፣ ተጨማሪ አገልግሎቶችን እና ነጻ የትምህርት ቤት ምግቦችን፤ ወደ መጀመሪያ እና ከመጀመሪያ ትምህርት ቤት መጓጓዣ እንዲያገኝ ልጅዎን ሊረዳ ይችላል፤ እናም የማህበረሰብ ድጋፎችን እንዲያገኙ እርስዎን ያግዛል።



- ልጅዎን በአዲስ ትምህርት ቤት ሲያስመዘግቡ፣ ከእሱ/ከእሷ **መምህር(ራን)** ጋር ለመገናኘት መጠየቅ አለብዎት። እንዲሁም እሱ ወይም እሷ እንዴት እየሰራ/ች እንደሆነ ለመነጋገር የልጅዎን አስተማሪ(ዎች) በየጊዜው መነጋገር አለብዎት። ስለልጅዎ የትምህርት ቤት ስራ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እና ልጅዎን ለመማር የሚረዳውን መረጃ ለመስጠት በልጅዎ ትምህርት ቤት ቢያንስ አንድ መምህር በደንብ ይወቁ።
- **የትምህርት ቤቱ አማካሪ** ልጅዎ ለውጦችን እና ፈተናዎችን እንዲቋቋም ሊረዳው ይችላል። ልጅዎ በቤት ውስጥ እንዴት እንደሚሰራ ወይም እሱ ወይም እሷ እያጋጠማቸው ስላለው የትምህርት ቤት ስራ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ስለሚችሉ ነገሮች ማንኛውንም መረጃ ለዚህ ሰው ያጋሩ።
- መታወቅ ያለባቸው ሌሎች ጥሩ ሰዎች የትምህርት ቤቱ **ርእሰ መምህር፣ ክትትል ኦፊሰር፣ የአውቶቡስ ሹፌር፣ የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሰራተኛ**፣ እና **የትምህርት ቤት ነርስ** ናቸው።
- **ሁሉም የትምህርት ቤት እና የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ሰራተኞች** ልጅዎ በትምህርት ቤት ጥሩ ለመስራት የሚያስፈልጉትን ሁሉንም አገልግሎቶች ማግኘቱን ማረጋገጥ ይችላሉ። በልጅዎ ትምህርት ውስጥ ጠቃሚ አጋር ነዎት እና ከትምህርት ቤት እና ከትምህርት ዲስትሪክት ጋር በቡድን መስራት አለብዎት።

## የማኪኒ-ቬንቶ ህግ ስር ስለ አገልግሎቶች ምን ጥያቄዎች መጠየቅ አለብኝ?

- የአካባቢው መጠለያ የሌላቸው የትምህርት ተጠሪ ማነው? እሱን ወይም እሷን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?
- ልጁ በዚያው ትምህርት ቤት (የመጀመሪያ ትምህርት ቤት) ለመቆየት ምን መጓጓዣ አለ?
- ልጁ ትምህርት ቤቶችን ከቀየረ፣ መዝገቦችን ወደ አዲሱ ትምህርት ቤት በፍጥነት እንድናስተላልፍ ማን ሊረዳን ይችላል?
- ልጁ በትምህርት ቤት ነፃ ምግብ እንዴት ማግኘት ይችላል?
- አስፈላጊ ከሆነ፣ ልጁ ነፃ የትምህርት ቁሳቁሶችን እንዴት ማግኘት ይችላል?
- ልጁ የልዩ ትምህርት አገልግሎት ቢፈልግ ማን ሊረዳው ይችላል? እነዚህ አገልግሎቶች በምን ያህል ፍጥነት ሊዘጋጁ ይችላሉ?
- ለልጁ ምን አይነት የአካዳሚክ እገዛ አለ፣ እንደ ርዕስ I ፕሮግራሞች ወይም ከትምህርት በኋላ ማስተማር?
- የልጁን ተሰጥኦ ለማዳበር እና ልዩ ፍላጎቶቹ/ቿን ለማሟላት ምን ፕሮግራሞች ሊረዱ ይችላሉ?
- ለልጁ ስፖርት፣ ሙዚቃ ወይም ሌሎች እንቅስቃሴዎች ይገኛሉ?
- ለእነርሱ መክፈል ካልቻልኩ፣ ልጁ ወደ ክፍል ጉዞዎች መሄድ ወይም በሌሎች የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች መሳተፍ እንዴት ይችላል?
- ለታናናሽ ልጆቼ የቅድመ ትምህርት ቤት ፕሮግራም አለ?





## ልጄን በትምህርት ቤት ለማገዝ ምን ማድረግ አለብኝ?

- ልጅዎ በየቀኑ ትምህርት ቤት መሄዱን እና አርፎና ተመግቦ መድረሱን ያረጋግጡ።
- ለልጅዎ የቤት ስራ እንዲሰራ ጸጥ ያለ ቦታ ይስጡ እና ልጅዎን በቤት ስራ ለመርዳት በየቀኑ ጊዜ ይመድቡ።
- ለልጅዎ የጤና ፍላጎቶች ትኩረት ይስጡ እና ማንኛውንም ችግር አስቀድመው ይቆጣጠሩ።
- በትምህርት ቤት ምን እየተማረ ወይም እየተማረች እንደሆነ ልጅዎን ይጠይቁ። እሱ ወይም እሷ እንዲገልጽልዎ/እንድትገልጽልዎ ያድርጉ። በልጅዎ ትምህርት ፍላጎት ካሳዩ፣ እሱ ወይም እሷ ትምህርቱ አስፈላጊ መሆኑን ያውቃሉ።



- በየቀኑ ለልጅዎ ያንብቡ። ለትላልቅ ልጆች፣ እርስዎ እና ልጅዎ በጸጥታ በጋራ እንድታነቡ በየቀኑ ጊዜ ይመድቡ። ስላነበቡት ነገር ይናገሩ።
- ጥሩ ውጤት እንደማግኘት ወይም በትምህርት ቤት የስፖርት ቡድን ውስጥ እንደመጫወት ላሉ ልጅዎ ለሚያደርገው/ለምታደርገው ጥሩ ነገር ያመስግኑ።

### ጥሩ ጥያቄዎች ጥሩ አንባቢዎችን ያወጣሉ

ልጆች ስለሚያነቡት ነገር መጠየቅ ጥሩ አሳቢ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል።

**ለታሪኮች (ልብወለድ)፦**

- ምንድን ነው የሆነው? ቀጥሎ ምን ይሆናል ብለህ/ሽ ታስባለህ/ቢያለሽ? ለምን?
- ዋናው ገፀ ባህሪ ማን ነው? እሱን/እሷን ትወዳለህ/ትወጃለሽ? ለምን? እሱ ወይም እሷ ያደረጉትን ታደርግ ነበር? ባይሆን ምን ታደርግ ነበር?
- ይህ ታሪክ ምን እንዲሰማህ/ሽ አደረገ?

**ለመረጃ ቁሳቁስ (ልብ ወለድ ያልሆኑ)፦**

- ጽሑፉ ወይም ምዕራፍ ስለ ምን ነበር? በተቻለ መጠን ብዙ ዝርዝሮችን ይጠይቁ።
- የደራሲው ዋና ነጥብ ምን ይመስልሃል?
- የትኛው ክፍል በጣም አስደሳች ሆኖ አግኝተሃል?
- ይህ መረጃ ለምን አስፈላጊ ነው ብለው ያስባሉ?

- ልጅዎ የሚያጋራዎትን ነገር እና እሱ ወይም እሷ ስላጋጠሙት/ስላጋጠማት ማናቸውም ችግሮች ሲናገር/ስትናገር ያድምጡ። ስለእነዚህ ችግሮች ከአስተማሪ ወይም ከትምህርት ቤት አማካሪ ጋር መነጋገር ይችላሉ።
- ልጅዎን እንደ ስፖርት እና ሙዚቃ ባሉ ነገሮች ላይ እንዲሳተፍ ያበረታቱት።

# ምንጮች ከ NCHE

## ከክፍያ ነጻ የእርዳታ መስመር፡- 800-308-2145 ወይም homeless@serve.org.

መጠለያ ለሌላቸው NCHE ልጅዎ በትምህርት ቤት ስላለው መብት ሊያብራራልዎና በእርስዎ ትምህርት ቤት የሚገኘውን የአካባቢው ተጠሪ እንዴት አድርገው ማግኘት እንደሚችሉ ሙሉ መረጃ ሊሰጥዎ ይችላል። የአካባቢው ተጠሪ ልጅዎን ትምህርት ቤት በማስገባትና ልጅዎ የሚያስፈልገውን እገዛ እያገኘ/ኘች መሆኑን በማረጋገጥ ረገድ ሊረዳዎ ይችላል።

## ድረ-ገፅ፡- http://nche.ed.gov

- የ NCHE ድረ-ገጽ ብዙ ጥሩ መረጃዎች አሉት፣ ልጃቸውን በትምህርት ቤት መርዳት የሚፈልጉ ወላጆች ድረ-ገጽን ጨምሮ፡- https://nche.ed.gov/ibt/parent_res.php።

## የወላጆች የመረጃ ማሰባሰቢያ ማህደር

- የወላጆች የመረጃ ማሰባሰቢያ ማህደር ከልጅዎ ትምህርት ጋር በተገናኘ ማናቸውንም ወረቀቶችና ጠቃሚ ሬከርዶች የሚያስቀምጡበት ማህደር ነው። በዚህ ማህደር ውስጥ መጠለያ የሌላቸው ልጆች ስላላቸው የትምህርት መብቶች የሚያብራራ ሰነድም ይገኝበታል።
- በ 800-308-2145 ላይ በመደወል ወይም https://nche.ed.gov/online_order.php በመጎብኘት እነዚህን ማህደሮች በነጻ ይዘዙ።

## የአካባቢ ተጠሪ

## መጠለያ ለሌላቸው የክልሉ የትምህርት አስተባባሪ

ይህ ሰነድ ብሔራዊ መጠለያ ለሌላቸው ትምህርት ማእከል ቋንቋ እና ቁሳቁሶችን በመጠቀም በህዝብ ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ ተዘጋጀ። ይህ ሰነድ በ Creative Commons CC-BY ስር የተጠበቀ ነው። ለበለጠ መረጃ፡ k12.wa.us ን ይጎብኙ

Washington Office of Superintendent of
**PUBLIC INSTRUCTION**

Amharic